የሰ.መ.ቁ.139969

መጋቢት 25 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡…1. ዳኜ መላኩ

2. ተኽሊት ይመሰል

3. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

4. ቀነዓ ቂጣታ

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች፡-የወረኢሉ ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋም ዓ/ሕግ ሙሉ ባይለየኝ ቀርበዋል

ተጠሪ፡-……….ንብ ኢንሹራንስ ኩባንያ የቀረበ የለም

ይህ መዝገብ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የቅድሚያ ክፍያ እና የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ዉል የሚመለከት ሲሆን ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.130618 በ8/5/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ መነሻ ሲታይ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአሁን አመልካች ተከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ጣልቃ ገብ፣ በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነዉ ሶያስ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከሳሽ ሁኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ከሳሽ ባቀረበዉ ክስ ከተከሳሽ ጋር ባድረግነዉ ዉል የቴክኒክና ስልጠና ተቋም ለማስገንባት ከሳሽ ሥራዉን የሰራ ቢሆንም ተከሳሽ በድምሩ ብር 708,271.42 ስላልከፈለኝ ይህን ገንዘብ እንዲከፍለኝ በማለት ከሷል፡፡

በዚህ ክስ ላይ ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ የግንባታዉ ዉል መደረጉ አይካድም፣ ከሳሽ የሰራዉን ሥራ ጥራት የጎደለዉ እና ብልሽት ያለበት ስለሆነ ተከሳሽ ኃላፊነት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ በሌላ በኩል ተከሳሽ ባቀረበዉ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ከሳሽ ግንባታዉን እንደዉሉ ሰርቶ ያላጠናቀቀ እና ያልፈጸመዉ ስለሆነ የዉል ማስከበር 357,692.85 እንዲከፍለን፣ ጣልቃ ገብ ደግሞ በቅድሚያ ክፍያ እና በመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ዉል መሰረት ባልተነጣጠለ ኃላፊነት አለበት፣ ሥራዉን በሌላ ተቋራጭ ለማሰራት የሚናወጣዉን ወጪ ለመጠየቅ መብት እንዲጠበቅልን በማለት ከሷል፡፡ በዚህ ክስ ላይ የሥር ከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ተከሳሽ ላቀረበዉ ክስ ኃላፊነት የለብንም ክሱ ዉድቅ ነዉ በማለት

ተከራክሯል፡፡ ጣልቃ ገብ ወደ ክርክሩ እንዲገባ ተደርጎ ባቀረበዉ መልስ ለከሳሽ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ለብር 917,502.11 መስጠቱን እና ዉሉ ሳይታደስ መቅረቱን እና የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ዉል ለብር 357,692.95 እስከ ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠ መሆኑን በመግለጽ፣ ከዋስትና ጊዜ ገደብ ዉጭ ሽፋን ላልሰጠበት ጊዜ ኃላፊነት የለብንም፣ ተከሳሽ የስራ ተቋራጩን የስራ ጉድለቶች ከበቂ ማስረጃ ጋር በጽሑፍ ለጣልቃ ገብ የማሳወቅ ግዴታዉን ያልተወጠ ስለሆነ ቅድመ ሁኔታዉ ባልተሟለበት ኃላፊነት የለብንም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤት ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ከሳሽ የሰራዉ ሥራ የጥራት ችግር ያለበት መሆኑ ተረጋግጦ ዉሉ በዚህ ምክንያት መቋረጡ በማስረጃ ተረጋግጧል፤ ጣልቃ ገብ የቅድሚያ ክፍያ እና የመልካም ሥራ አፈጻጸም ለከሳሽ የዋስትና ሽፋን መስጠቱን አልካደም፣ የዋስትና ዉሉን የማደስ ኃላፊነት የተከሳሽ ሳይሆን የከሳሽ ነዉ፤ ከሳሽ የጠየቀዉ አረቦን ለተከፈለበት ጊዜ እንጂ ላልተከፈለበት ጊዜ አልጠየቀም፤ ስለዚህ ከሳሽ እና ጣልቃ ገብ በጋራ ብር 316,168.11 (ሶስት መቶ አስራ ስድስት ሺህ መቶ ስልሳ ስምንት አስራ አንድ ሳንቲም) ለተከሳሽ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የሥር ጣልቃ ገብ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ መልስ ሰጭ በዋስትና ዉሉ መሰረት የስራ ተቋራጩ በሥራዉ ላይ ችግር የፈጠረ ወይም ጥፋት መፈጸሙን ለይግባኝ ባይ በወቅቱ በጽሑፍ ያሳወቀ መሆኑን ማስረጃ የለም፤ በመሆኑም መልስ ሰጪዉ የራሱን ተነጻጻር ግዴታ ባልተወጣበት ይግባኝ ባይ ግዴታዉን እንዲወጣ መጠየቅ አይችልም፤ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ዉል መታደስ ከነበረበት ከ7 ወር በኋላ መልስ ሰጪዉ ክስ ያቀረበ ስለሆነ የሥር ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት የሥር ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ21/7/2009 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ የዋስትና ዉሉ እስከ ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ.ም የሚቆይ ሲሆን ከዚህ ጊዜ በኋላ የእድሳት ጊዜ አንድ አመት ስለሆነ ጊዜዉ የሚያልቀዉ ግንቦት 17 ቀን 2004 ዓ.ም በመሆኑ፣ አመልካች ይህ ጊዜ ሳይደርስ ክስ ያቀረበ ሆኖ ሳለ፣ ተጠሪ በቅድሚያ ክፍያ እና በመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ዉል መሰረት የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት የይጋርዉ ጊዜ ደግሞ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.47004 ላይ በሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1845 መሰረት አስር ዓመት ሆኖ ሳለ፣ የፌዴራል ጠቅላይ

ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልን፣ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልን በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የሥር ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ጊዜዉ ስላልተራዘመ ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም የመባሉን አግባብነት ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.1845 አንጻር፣ ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት ሐምሌ 14 ቀን 2009 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ የሰጠዉ ዉሳኔ ግንባታና የዋስትና ዉሎችን መሰረት ያደረገ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ እንዲጸናልን በዚህ ክርክር ምክንያት የደረሰብን ወጪና የጠበቃ አበል አመልካች እንዲከፍለን እንዲወሰንልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉ ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንዲሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ በአመልካች እና በሥር ከሳሽ ሶያስ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር መካከል በተደረገዉ የግንባታ ዉል መሰረት ለመፈጸም የአሁን ተጠሪ የሰጠዉን የቅድሚያ ክፍያ እና የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና በማቅረብ እንደሆነ ግራ ቀኛቸዉ ያልተካካዱት ጉዳይ ነዉ፡፡ የሥር ከሳሽ የግንባታዉን ሥራ 53.47% ብቻ ሰርቶ ሥራዉን ሳይቀጥል ጥሎ እንደሄዳ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ አሁን ለክርክር ምክንያት የሆነዉን የአሁን አመልካች ባቀረበዉ የዳኝነት ጥያቄ የሥር ከሳሽ በግንባታዉ ዉሉ መሰረት ግንባታዉን ሥራ ስላልፈጸም ከሳሽ ዉል ማስከበሪያዉ እንዲከፍለን፣ የአሁን ተጠሪ ደግሞ አመልካች በዋስትና ዉሎቹ መሰረት የከሳሽን የሥራ ጉድለቶች በጽሑፍ ከበቂ ማስረጃዎች ጋር ለተጠሪ ያስታወቁ ነገር የለም፣ ይህ ቅድመ ሁኔታ ባልተሟለበት ኃላፊነት የለብንም በማለት መከራከራቸዉን ያሳያል፡፡

በዚህ ረገድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የሥራ ተቋራጩን የሥራ ጉድለቶች በወቅቱ ለተጠሪ በጽሑፍ ከበቂ ማስረጃ ጋር ያለ ማሳወቁን በማረጋገጥ፣ አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1757 መሰረት የራሱን ተነጻጻሪ ግዴታዉን ሳይወጣ ተጠሪ ግዴታዉን እንዲወጣ መጠየቅ አይችልም በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ቅሬታ የሥራ ተቋራጩ በሥራ ላይ የፈጸመዉን ጉድለቶች ወይም በዉሉ መሰረት አለመፈጸሙን በወቅቱ በጽሑፍ ከበቂ ማስረጃ ጋር ለተጠሪ

ያሳወቀ ነገር መኖሩን ገልጾ የተከራከረዉ ነገር የለም፡፡ አመልካች በቅሬታዉ የሥራ ተቋራጩ በሥራዉ ላይ የፈጠረዉን ጉድለቶች በወቅቱ በጽሑፍ ለተጠሪ ማሳወቁን የገለጸዉ ነገር የለም፡፡ ይህ በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ሲሆን በሕጉ አግባብ እንደሚከተለዉ መርምረነዋል፡፡

በሲቪል ግንባታ ሥራ ፕሮጀክቶች የዉል ሁኔታዎች መመሪያ አንቀጽ 10 ሥር የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ተመልክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ሥር እንደተመለከተዉ ‹‹የሥራ ተቋራጭ ጨረታዉን ስለማሸነፉ ተቀባይነት ያገኘበትን ደብዳቤ በተቀበለ በ30 ቀናት ዉስጥ የዉል ዋጋዉ 10% የሆነዉን መጠን ዉሉን በአግባቡ እና በአግባቢ ለማወከናወንና ሁሉንም ድንጋጌዎች፣ ስምምነቶች፣ ሁኔታዎች እና በዉል በተመለከቱት ነገሮችን ለመጠበቅና በዛ አግባብ ለመፈጸም የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ወይም ቦንድ ማቅረብ እንዳለበት፡፡ የዋስትናዉ ቅርጽና ይዘት አጠሪዉ እና የሥራ ተቋራጩ እንደተስማሙ ሊሆን እንደሚችል ነዉ፡፡ የሥራ ተቋራጭ በጨረታ ሰነድ በተመለከተዉ ቦታ ላይ የዋስትና ሰጪዉ (Surety) ስም መሙላት እንዳለበት ነዉ፡፡›› ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የግንባታ ሥራ ለማከናወን የሥራ ተቋራጩ ሊያቀርብ ከሚገባቸዉ አስፈላጊ ነገሮች መካከል አንዱ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ የዋስተናዉ ዓላማም የሥራ ተቋራጩ በግንባታ ዉሉ እና የዚህ ዉል አካል በሆኑት ሰነዶች በተመለከተዉ አግባብ ሥራዉን ለማከናወን መተማመኛ ወይም ዋስትና የሚያቀርብበት ሁኔታ ነዉ፡፡ የዉሉን ይዘትና ቅርጽ በተመለከተ አስገዳጅነት ያላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ አሰሪዉ እና የሥራ ተቋራጩ በነጻነት እንዲስማሙ መብት ሰጥቷቸዋል፡፡

እንደሚታወቀዉ ከግንባታ ሥራ ጋር በተያያዘ ከአደጋ አስተዳደር እስትራቴጅ ዉስጥ ዋናዉ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ነዉ፡፡ የዋስትናዉም ዓላማ ገዢዎችን እና ኢንቨስተሮችን ከሥራ ተቋራጩ እንደዉሉ ባለመፈጸም ምክንያት የሚደርሰዉን አደጋ ለመከላከል ነዉ፡፡ በዋስትናዉ ተጠቃሚ ለመሆን አሰሪዎች በቦንዱ እና በዉሉ የተመለከቱትን ግዴታዎች በመገንዘብ በዚህ አግባብም መፈጸማቸዉን የማረጋገጠ ኃላፊነት አለበት፡፡ ዋስትናዉን መሰረት በማድረግ የመብት ጥያቄ ለማቅረብ አሠሪዉ የሥራ ተቋራጩ እንደዉሉ፣ በዉሉ ቃሎች እና ሁኔታዎች መሰረት አለመፈጸሙን በጽሑፍ ለዋስትና ሰጪዉ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡ አሠሪዉ በዚህ አግባብ የፈጸመ እንደሆነ፣ በመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትናዉ መሰረት የመብት ጥያቄ ለዋስትና ሰጩዉ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ዋስትና ሰጪዉ የመብት ጥያቄዉን እንደተቀበለ የጥያቄዉን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ምርመራ ያደርጋል፡፡ በዚህ ምርመራ ዋስትና ሰጪዉ ለማረጋገጥ የሚጥረዉ ሁለቱም ማለትም አሠሪዉ እና የሥራ ተቋራጩ በዉሉ እና በዋስትናዉ የተመለከቱትን ግዴታዎቻቸዉን መወጣት አለመወጣታቸዉን ነዉ፡፡ ዋስትና ሰጪዉ በዚህ አግባብ

ምርመራ ካደረገ በኋላ ያሉት ምርጫዎች ከአሠሪዉ ጋር በመነጋገር የሥራ ተቋራጩ ሥራዉን የሚቀጥልበትን ሁኔታ ይወስናሉ፤ ዋስትና ሰጪዉ ራሱ ሥራዉን ለማጠናቀቅ ከአሠሪዉ ጋር ዉል ይፈጽማል፤ ዋስትና ሰጪዉ ከአሠሪዉ ጋር በመነጋገር ሌላ የሥራ ተቋራጭን ተክቶ ሥራዉ የሚጠናቅቅበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ ወይም ዋስትና ሰጪዉ በዋስትናዉ እስከ ተመለከተዉ ገንዘብ ለአሠሪዉ ወጪ ለመክፈል ይወስናል ማለት ነዉ፡፡

ከዚህ አንጻር ዋስትና /suretyship/ የሚመለከቱ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1920 እስከ 1951 ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት እንዳላቸዉ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1920 እንደሚደነግገዉ ለግዴታዉ አፈጻጸም ዋስ የሚሆን ሰዉ ባለዕዳዉ ግዴታዉን ያልፈጸመ እንደሆነ ለባለገንዘቡ ይህን ግዴታ ሊፈጽም ይገደዳል፡፡ በማለት ደንግጓታል፡፡ የዋስትና ሰጪዉ ግዴታ ከዋናዉ ባለዕዳ በላይ ሊከፍል እንደማይገባዉ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1924 ይዘት ያስገነዝባል፡፡ ዋስትና ሰጪዉ ከዋናዉ ባለዕዳ ጋር የአንድነት የሆነ ዋስትና የገባ እንደሆነ በአንድነትና በነጠላ መጠየቅ እንደሚችሉ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1933 ያመለክታል፡፡

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች የሥራ ተቋራጩን የሥራ ጉድለቶች በወቅቱ ለተጠሪ አለመሳወቁ በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ከመሆኑም በላይ አመልካች ይህን ሁኔታ ለተጠሪ የማሳወቅ ጉዳይ እንደግዴታዉ በመቁጠር ያቀረበዉ ክርክር የለም፡፡ ነገር ግን የአሁን ተጠሪ በሰጠዉ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና (performance bond) መሰረት አመልካች የማካካሸ መብቱን ለመጠየቅ የሚችለዉ በዋስትናዉ የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች (conditions precedent) ሲያሟላ ብቻ እንደሆነ ሰነዱ ያመለክታል፡፡ ይህም በዋስትነዉ አንቀጽ 1 ሥር እንደተመለከተዉ አሠሪዉ ወይም የአሰሪዉ ተወካይ ኪሳራን የሚያስከትል ማንኛዉም ድርጊት ወይም አለማድረግ መከሰቱን ያረጋገጠ እንደሆነ፣ ወዲያዉኑ በጽሑፍ በቂ መረጃ ለዋስትና ሰጨዉ በዋናዉ መ/ቤት ወይም በቅርንጫፍ ጽ/ቤት የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡ በዋስትናዉ አንቀጽ 2 መሰረት የሥራ ተቋራጩ እንደዉል ስምምነቱ ድንጋጌዎች ሥራዉን ሊያከናዉን ያልቻለ እንደሆነ የሥራ ዉሉ እንዳልተሳካ ተቆጥሮ ዋስትናዉ የዉሉን ቀሪ ሥራዎች በራሱ አማራጭ የማከናወን ወይም ለንዑስ ተቋራጭ የመስጠት አማራጭ እና መብት ይኖረዋል፡፡

በሌላ በኩል የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ወይም ቦንድ (Advance Payment Bond) ሥር የተመለከቱት አሠሪዉ መብቱን ለመጠየቅ ሊሟሉ የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች (conditions precedent) እንዳሉ ማየት ይቻላል፡፡ ከእነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች በቁጥር 1 የዋስትናዉ ኦሪጅናል ሰነድ የዋስትናዉ ጊዜ እንዳበቃ ለዋስትና ሰጨዉ መመለስ አለበት፤ የዋስትናዉ ማለቂያ ቀን ወይም ከማለቁ በፊት ዋስትና ሰጨዉ

ከአሠሪዉ ምንም የመብት ጥያቄ ያልተቀበለ እንደሆነ ሰነዱ ለዋስትና ሰጪዉ እንደተመለሰ ወይም ባይመለስም ዋስትናዉ ዋጋ ያለዉም፡፡ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ቁጥር 2 ሥር ደግሞ በመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ቁጥር 1 ሥር የተመለከተዉ ሁኔታ ተቀምጦ እናገኛለን፡፡ በዚህ በቅድሚያ ክፍያ ዋስትና መሰረት የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልቶ ለዋስትና ሰጪዉ የተገለጸ እንደሆነ በቅድሚያ ክፍያ ዋስትና አንቀጽ 3 ሥር የተመለከቱትን እርምጃዎች መዉሰድ ይችላል ማለት ነዉ፡፡

ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለዉ የአሁን አመልካች በእነዚህ የዋስትና ዉሎች መሰረት የመብት ጥያቄ በተጠሪ ላይ ለማቅረብ በዉሎቹ የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች (conditions precedent) በበኩሉ መፈጸም ወይም መወጣት ይጠበቅበታል፡፡ የአሁን አመልካች እነዚህ ዉሎች የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች በራሱ በኩል ያልፈጸመ እንደሆነ የተጠሪን መብት የሚያጣብብ እና የሚጎዳ በመሆኑ፣ ተጠሪ ግዴታዉን እንዲወጣ ለመጠየቅ የሚችልበት ሁኔታ የለም፡፡ በመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና መሰረት የአሁን አመልካች የሥራ ተቋራጩ የሥራ ጉድለቶችን ለተጠሪ ያላሳወቀዉ እንደሆነ፣ ተጠሪ በዋስትናዉ አንቀጽ 2 ሥር የተመለከቱትን አማራጮች ፈትሾ የሚያዋጣዉን እርምጃ እንዳይወስድ የሚያደርግና መብቱን የሚያጣብብ እና ያለ አግባብ ተጎጂ እንዲሆን የሚያደርገዉ ነዉ፡፡ ስለሆነም የአሁን አመልካች የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ላይ በተመለከተዉ መሰረት ቅድመ ሁኔታዎቹን አልፈጸመም ማለት የራሱን ግዴታ አለመወጣቱን የሚያሳይ በመሆኑ፣ ተጠሪ ደግሞ ግዴታዉን እንዲወጣ የሚጠይቅበት አግባብ የለም፡፡ በዚህ ረገድ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1757 መመልከት ይቻላል፡፡

የአሁን አመልካች ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ መሰረት ግዴታዉን ቢወጣ ኖሮ በዋስትናዉ መሰረት መብቱን ለመጠየቅ የሚያስችለዉን መብት አቋቁሟል ማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን አመልካች በዚህ መሰረት የሥራ ተቋራጩን የሥራ ጉድለቶች ለተጠሪ በጽሑፍ ያስታወቀዉ ነገር ስለሌለ እና የበኩሉን ግዴታ ያልተወጣ ስለሆነ፣ መብቱን አቋቁሟልና ተጠሪን መጠየቅ ይችላል የሚያስብል ነገር የለም፡፡ አመልካች በዋስትናዉ መሰረት መብቱን ለመጠየቀ የሚያስችለዉን መብት አቋቁሞ ቢሆን ኖሮ፣ ይህን መብቱን ካቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በሰ.መ.ቁ.47004 ላይ በተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1845 መሰረት በአስር ዓመት ጊዜ ዉስጥ መብቱን ካልጠየቀ በይርጋ ሊያጣ ይችላል፡፡ ነገር ግን በሰ.መ.ቁ.47004 ላይ አሠሪዉ የሥራ ተቋራጩን የሥራ ጉድለቶች ለዋስትና ሰጪዉ ያለማሳወቅ ጉዳይ እንደጭብጥ ተይዞ ክርክር ተደርጎበት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ሁኔታ የለም፡፡ አሁን በተያዘዉ ጉዳይ ደግሞ አሠሪዉ የሥራ ተቋራጩን የሥራ ጉድለቶች ለዋስትና ሰጪዉ ያለማሳወቅ ጉዳይ እንደጭብጥ ተይዞ ለዉሳኔዉ መሰረት እንደሆነ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህ ከሆነ በሰ.መ.ቁ.47004 እና አሁን በተያዘዉ ጉዳይ

ተመሳሳይ ጭብጥ የሌላቸዉ ስለሆነ፣ የሰ.መ.ቁ.47004 ላይ የተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በዚህ ጉዳይ ላይ ተፈጻሚነት የለዉም ብለናል፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካች የራሱን ግዴታ ባልተወጣበት ተጠሪዉ በዋስትናዉ መሰረት ግዴታዉን እንዲወጣ የመጠየቅ መብት የለዉም፡፡

ሲጠቃለል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአሁን አመልካች ያቀረበዉን የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ በሕግ አግባብ የተሰጠ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት ስለማይቻል የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.130618 በ08/5/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በዉጤት ደረጃ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
3. ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
4. ይህ ዉሳኔ በ3/8/2010ዓ.ም ተነብቧል

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞ ፊርማ አለበት**

**ቤ/ፍ**